# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. /// አዘጋጅ መላኩ ማሞ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org

ሚያዝያ 1996 Apr 2004 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።” (ኢሳ 54 ÷ 13)

# ቤተ ክርስቲያንና እስራኤል

አምላካችን እግዚአብሔር የማዳን ሥራውን መግለጽ ሲጀምር የጠራው አብርሃምን ነበር። የዕምነት አባትና የአይሁድ አባት የሆነው አብርሃም የተጠራበት ጥሪ እንደሚከተለው ተጽፎአል።

“እግዚአብሔርም አብራምን አለው ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ፤ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ ÷ እባርክህ ማለሁ÷ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤የሚባርኩህንም እባርካለሁ÷ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።” (ኦሪት ዘፍጥረት 12÷1-3)

በኦሪት ዘፍጥረት 15 ÷ 6-21 ደግሞ የከነዓን ምድር ለአብራምና ለዘሩ መሰጠቱን እናነባለን።

“አብራምም በእግዚአብሔር አመነ÷ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ እንድሰጥህ ከከለዳውያን ዑር ያወጣሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለው።” (ኦሪት ዘፍጥረት 15÷6-7)

ይህችም ምድር እስራኤል ናት። የቤተ ክርስቲያን ራስና የምድር ነገዶች ሁሉ በረከት የሆነው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተወለደው ከእስራኤል ነው። ክርስትናችንን ወደ ዓለም ሁሉ ለማዳረስ ነፍሳቸውን የሰውት ሐዋሪያቱ እስራኤላውያን ናቸው።

ጌታ እየሱስ ራሱ “…መዳን ከአይሁድ ነውና…” ሲል ዕውነተኛ የእግዚአብሔር አምልኮ በእስራኤል መጀመሩን ያስረዳል። (የዮሐንስ ወንጌል 4÷22)

ሐዋሪያው ጳውሎስም “ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ አንተም የበረሀ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ÷በቅርንጫፎች ላይ አትመካ ፤ ብትመካባቸው ግን ሥሩ አንተን ይሸከመሃል እንጂ ሥሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም።” ሲል ስለ አይሁድ ሊኖረን የሚገባንን አመለካከት ያስተምረናል። (ወደ ሮሜ ሰዎች 11÷17-18)

**የእግዚአብሔር ሕግና ቃሉ የመጣልን ከእስራኤል ነው።**

“ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና ብዙዎች አሕዛብ ሄደው፦ ኑ÷ወደ እግዚአብሔር ተራራ÷ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል÷በጎዳናውም እንሄዳለን ይላሉ።” (ትንቢተ ኢሳይያስ 2÷3)

እንዲሁም፦ “እግዚአብሔር ትልቅ ነው፤ በአምላካችን ከተማ በተቀደሰው ተራራ ምስጋናው ብዙ ነው። በሰሜን ወገን በመልካም ሥፍራ የቆመ የምድር ሁሉ ደስታ የጽዮን ተራራ (እስራኤል) ነው፤ እርሱም የትልቁ ንጉሥ (የጌታ እየሱስ) ከተማ ነው።” ይላል (መዝሙረ ዳዊት 48÷1-2)

ደግሞ መዝሙረ ዳዊት 122 “ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ፤ አንተንም ለሚወዱ ልማት ይሁን። በኃይልህ ሰላም÷በጌጠኛ ቤትህም ልማት ይሁን። ስለ ወንድሞቼ ስለ ባልንጀሮቼም፦ በውስጥሽ ሰላም ይሁን አልሁ። ስለ አምላካችን ስለ እግዚአብሔር ቤት ላንቺ መልካምነትሽን ፈለግሁ።” ይላል (መዝሙረ ዳዊት 122 ÷ 6 - 9)

ጌታ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን የተስፋ ቃል ወደ ፍጻሜ ያመጣል። እስራኤልም መንፈሳዊ ዓይኖቿ ተከፍተው ላት÷መሲሑን አዳኝ÷እየሱስ ክርስቶስን ትቀበላለች። መንፈሳዊ ሥፍራዋንም ትይዛለች። በዚያን ጊዜ የሚወዷትና የሚባርኳት ሲደሰቱ÷ የሚረግሟት ግን “ወየው÷አላወቅንም ነበር” ይላሉ። ይህም የሚሆነው እስራኤል ከሰዎች የተሻሉ ሆነው አይደለም። ነገር ግን ጌታ እግዚአብሔር የምድር ነገዶችን ሁሉ ለመባረክ የነበረውን ዓላማ በጀመረበት ጊዜ እንደ ተናገረው በመጽሐፍም እንደ ተጻፈው÷ ቃሉ ሁሉ መፈጸም ስላለበት ነው።

ጌታ በነቢዩ ሕዝቅኤል የተናገረውን ተመልከቱ፦ “… እነሆ÷ የእስራኤልን ልጆች ከሄዱባቸው ከአሕዛብ መካከል እወስዳቸዋለሁ፡ ከሥፍራም ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ፡ወደ ገዛ ምድራቸውም አመጣቸዋለሁ ፤ በምድርም ላይ በእስራኤል ተራሮች ላይ አንድ ሕዝብ አደርጋቸዋለሁ÷… ከዚያ ወዲያም በጣዖቶቻቸውና በርኵሰታቸው በመተላለፋቸውም ሁሉ አይረክሱም÷ኃጢአትም ከሠሩባት ዓመፅ ሁሉ አድናቸዋለሁ፡ አነፃቸውማለሁ፤ ሕዝብም ይሆኑኛል፡እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ። … አባቶቻቸውም በኖሩባት ለባሪያዬ ለያዕቆብ በሰጠኋት ምድር ይኖራሉ፤ እነርሱና ልጆቻቸው፡ የልጅ ልጆቻቸውም ለዘላለም ይኖሩባታል÷ … የሰላምም ቃል ኪዳን ከእነርሱ ጋር አደርጋለሁ÷ የዘላለምም ቃል ኪዳን ይሆንላቸዋል፤ እኔም እባርካቸዋለሁ፡ አበዛቸውማለሁ ፡ መቅደሴንም ለዘላለም በመካከላቸው አኖራለሁ። ማደሪያዬም በላያቸው ላይ ይሆናል፤ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ፡ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል። መቅደሴም ለዘላለም በመካከላቸው በሆነ ጊዜ÷እኔ እስራኤልን የምቀድሰው እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ አሕዛብ ያውቃሉ።” (ትንቢተ ሕዝቅኤል 37÷21-28)

የጌታ እግዚአብሔር ክብር እንደገና በታላቅ ክንድ ወደ እየሩሳሌም ስለ መመለሱ ትንቢተ ኢሳይያስ እንዲህ ይላል፦ “ጽዮን ሆይ÷ ተነሺ÷ ተነሺ÷ ኃይልሽን ልበሺ፤ቅድስቲቱ ከተማ እየሩሳሌም ሆይ÷ ያልተገረዘና ርኵስ ከእንግዲህ ወዲህ አይገባብሽምና ጌጠኛ ልብስሽን ልበሺ። እየሩሳሌም ሆይ÷ ትቢያን አራግፊ፤ ተነሺ ተቀመጪ፤ ምርኮኛዪቱ የጽዮን ልጅ ሆይ÷ የአንገትሽን እስራት ፍቺ። … እነሆ÷ጉብኞችሽ ጩኸዋል፤ እግዚአብሔር ወደ ጽዮን በተመለሰ ጊዜ ዓይን በዓይን ይተያያሉና ድምጻቸውን ያነሣሉ÷በአንድነትም ይዘምራሉ። እናንተ የእየሩሳሌም ፍርስራሾች ሆይ ÷ እግዚአብሔር ሕዝቡን አጽናንቶአልና÷ እየሩሳሌምንም ታድጎአታልና ደስ ይበላችሁ ÷ በአንድነትም ዘምሩ ። እግዚአብሔር የተቀደሰውን ክንዱን በአሕዛብ ሁሉ ፊት ገልጧል÷ በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ የአምላካችንን መድኃኒት ያያሉ።” (ትንቢተ ኢሳይያስ 52÷1-10)

እንግዲህ ወገኖቼ÷ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ፍጻሜና ሙላት በትዕግሥት የሚጠባበቁ ቅዱሳን ማሕበር አይደለችምን? የተስፋ ቃሉስ ፍጻሜ የደኅንነታችን ፍጻሜ አይደለምን?

መጥምቁ ዮሐንስ በእናቱ ማሕፀን ሳለ የጌታ እናት ድንግል ማሪያም ወደ ዮሐንስ እናት በቀረበች ጊዜ÷ ከእናቱ ሆድ ውስጥ ተንቀሳቀሰ። ምክንያቱም በማሪያም ሆድ የነበረው እየሱስ ከዮሐንስ ሕይወት ዓላማ ጋር የተያያዘ ስለ ነበረ ነው። ቤተ ክርስቲያንና እስራኤልም እንዲሁ ነን። እግዚአብሔር ይመስገን።

ስለዚህ ÷ ስለ እስራኤል የተነገሩት ትንቢቶች ወደ ፍጻሜ እየገሰገሱ ስናይ የቤተ ክርስቲያን ልብ መንቀሳቀስ ይኖርበታል። በጸሎት ሆነ በተግባር፦ እንደ ባለጉዳይ ሊያገባን ይገባል። ለጊዜው ጌታን ባለመቀበላቸው ምክንያት በጉዳያቸው የማያገባን ይመስል ተመልካች ብቻ መሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን፦ እስራኤል የሠላምዋን ጌታና አዳኝዋን ÷ እየሱስን ፈጥና እንድትቀበል መፀለይ፦

ሕዝብዋን ከተበተነበት ከዓለም ሁሉ መልሶ በሐገሩ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት መተባበር፦

ከአሸባሪዎችና ከጠላቶቿ በሚደረግባት ተቃውሞ አስፈላጊውን ሞራላዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ በመስጠት፦

ቤተ ክርስቲያንንና እስራኤልን በሚመለከት የተማታና ግራ የተጋባ ግንዛቤ ወይም የሐሰት ትምሕርት እንዳይኖር የጠራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምሕርትን ተምሮ በማስተማር፦ ንጉሣችን እየሱስ እስኪገለጥ ድረስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ግዴታችንን መወጣት ይጠበቅብናል።

## “ለእየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ”

(መዝሙረ ዳዊት 122÷6)

የፖስታ ወጪአችንን ለተጠቃሚዎችና ለሚፈልጉት ብቻ ማዋል÷ ስላለብን ቅነሳ ልናደርግ ነው። ደብዳቤአችን እንዳይቋረጥባችሁ የምትሹ ሁሉ÷ በዚህ ወር አሳውቁን። የፖስታ ቴምቤር በአሜሪካን ውስጥ በዓመት $4.44 ሲሆን በዓለም ዓቀፍ ደግሞ $9.60 USD ብቻ ነው። በአፍሪካ ለሚኖሩ ወገኖች መላክያ እስፖንሰር የሆናችሁ ጌታ ይባርካችሁ።ጌታ የሚያሳስባችሁ ፀልዩልን። ተባበሩን።

# የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና

ጌታችን እየሱስ ወደ ኢያሪኮ ገብቶ ያልፍ ነበር፡፡ “እነሆም ዘኬዎስ የሚባል ሰው፥እርሱም የቀራጮች አለቃ ነበረ፥ባለ ጸጋም ነበረ፡፡ እየሱስንም የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱም አጭር ነበረና ስለ ሕዝቡ ብዛት አቃተው፡፡ በዚያችም መንገድ ሊያልፍ ዘንድ አለውና ያየው ዘንድ ወደ ፊት ሮጦ በአንድ ሾላ ላይ ወጣ፡፡እየሱስም ወደዚያ ሥፍራ በደረሰ ጊዜ፥አሻቅቦ አየና፦ ዘኬዎስ ሆይ፥ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው፡፡ ፈጥኖም ወረደ፡ በደስታም ተቀበለው፡፡ … እየሱስም … ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፡ የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና፡ አለው፡፡” የሉቃስ ወንጌል 19፥1-10

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 እንደ ምንረዳው የጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ተልዕኮ ሦስት ገጽታዎች አሉት፡፡

## የሚጠፉት ብዛት፦

“መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ፥ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤ ወደ ቤትም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ፦ የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል፡፡” (ሉቃስ 15፥3-7)

የዚህ ምሳሌ ፍሬ ነገር ፥ የበጎቹ ባለቤት ከበጎቹ አንዱ መጥፋቱን በተረዳ ጊዜ ፥ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ ትቶ ፥ ፈጥኖ ፍለጋ መሄዱ ነው፡፡ ይህም ማለት እያንዳንዱ በግ በነፍስ ወከፍ፦ ተወዳጅና ተፈላጊ መሆኑ ነው፡፡ “ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል፡፡” (2 ጴጥሮስ 3፥9)

እውነቱ እንዲህ ነው፡፡በምድር ላይ የጠፋህ አንድ አንተ ብቻ ብትሆን እንኳ ኖሮ ፥ ጌታ እየሱስ መጥቶ በሞተልህ ነበር ፡፡ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር እያንዳንድዋ ነፍስ እጅግ የተወደደች ስለ ሆነች ነው፡፡ በማቴዎስ ወንጌል 10፥29 ከሁለት ድንቢጦች አንዲቱ “ያለ አባታችሁ (ያለ እግዚአብሔር) ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም” ተብሏል፡፡ በሉቃስ ወንጌል 12፥7 ደግሞ “የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ የተቈጠረ ነው፤” ይላል፡፡ ከፍ ሲል በጠቀስነው በ2ኛ ጴጥሮስ 3፥9 ደግሞ “ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል” ይላል፡፡

በምድር ላይ የሚገኙ ስድስት ቢሊዮን ሰዎች እያንዳንዳቸው በጌታ በእግዚአብሔር ዘንድ የተቈጠሩና በስማቸው የታወቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ፡ በዮሐንስ ራዕይ 3፥20 “እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ፡ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ፡ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፡ እርሱም ከእኔ ጋር” ያለው አንተን አስቦ ነው፡፡ ጌታ እየሱስ ያን ሁሉ መከራ የተቀበለው በነፍስ ወከፍ፥ ለእኔና ለአንተ ብሎ ነው፡፡

## ጌታ ለሚጠፉት ይገደዋል፦

ቀጥሎም እየሱስ እንዲህ አለ፥ “አሥር የወርቅ መሐለቅ ያላት ሴት አንድ መሐለቅ ቢጠፋባት ምን የምታደርግ ይመስላችኋል? መብራት አብርታ፥ቤቷን ጠርጋ እስክታገኘው ድረስ በየሥርቻው አጥብቃ ትፈልግ የለምን? ባገኘችውም ጊዜ ወዳጆችዋንና ጐረቤቶችዋን በአንድነት ጠርታ 'የጠፋውን መሐለቄን አግኝቼው ደስ ብሎኛልና ደስ ይበላችሁ!' ትላቸዋለች፡፡” (የሉቃስ ወንጌል 15፥ 8-9 አዲሱ ትርጉም)

በመጀመሪያ ያየነው ምሳሌ በቁጥር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይኸውም ከመቶ አንድ እንኳ ቢጠፋ ለባለቤቱ እጅግ አሳሳቢ መሆኑ ነው፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ግን ትኩረቱ በአፈላለጉ ብርታትና በጥንቃቄው ላይ ነው፡፡ ገንዘቧ በጠፋባት ሴት ምሳሌ ላይ፥ሴትየዋ ገንዘብዋን ለማግኘት የወሰደቻቸውን ሦስት ጠቃሚ ርምጃዎች ጌታ ሲያስተምረን እናስተውል፦

(1ኛ) “መብራት አብርታ፥

(2ኛ) ቤቷን ጠርጋ

(3ኛ) እስክታገኘው ድረስ በየሥርቻው አጥብቃ ትፈልግ የለምን?” (የሉቃስ ወንጌል 15 ፥ 8)

እንዲህ ላለ አፈላለግ ከሁሉ የሚሻል ምሳሌ ጌታ እየሱስ ራሱ ነው፡፡ የወንጌልን መጻሕፍት ስናነብ የምንረዳው ጌታችን እየሱስ የጠፉትን ፈልጎ ለማዳን ያደረገውን ጥንቃቄና ልፋት ነው፡፡ ከሥፍራ ሥፍራ በመዞር የሰዎችን ጥያቄዎች መለስ፥ ተዓምራት አደረገ፥ ተቃውሞን ታገሰ፥ ተስፋ ሳይቆርጥ ፈለገን፡፡ ተስፋ ሳይቆርጥ ፈልጎ ያገኘን ተከታዮቹ ሁሉ በምሥጋና የምንገዛለት ለዚህ ነው፡፡

## ጌታ ለጠፉት ይራራል፦

የሉቃስ ወንጌል 15፥11-32 አንድ ሰው ከነበሩት ሁለት ልጆች ስለ ታናሹ ልጅ ያወሳል፡፡ 'የጠፋው ልጅ' ምሳሌ የተባለው ነው፡፡ (አንብቡት) በዚህ ምሳሌ በቁጥር 20 አስደናቂው የእግዚአብሔር ርኅራኄ ይታያል፡፡ (ልጁ) “ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ፡፡ እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው፡፡” ልጁ ከአባቱ ንብረት ድርሻውን ተቀብሎ የሄደ አመፀኛ መሆኑ ቢታወቅም፥ አባትነውና፦ በፍቅር የልጁን መመለስ ይጠባበቅ ነበር እንጂ በቁጣና በመዓት አይደለም፡፡ ዛሬ እግዚአብሔርን የምናመልክ ክርስቲያኖች ምሕረቱን ሳንቀበል ስንት ዘመን በዓመፅ አሳለፍን? ቢሆንም ተጸጽተን በተመለስን ጊዜ ጌታ በተዘረጉ እጆች ተቀበሎ ማረን እንጂ በቁጣ ፊቱን አላዞረብንም፥ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

ጌታ እየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰበት ጊዜ ለእያንዳንዱ ነፍስ ይገደው ነበር፡፡ በታላቅም ጥንቃቄ የጠፉትን ይፈልግ ነበር፡፡ለሚጠፉት ነፍሳት ርኅራኄ ነበረው፡፡ዛሬም ያው ነው፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

አንተን አግኝቶህ ይሆን? አንቺስ? ጌታ ፍለጋውን አቋርጦ አያውቅም፡፡ ቢሆንማ ኖሮ ይህ ደብዳቤ ባልደረሰህ ነበር፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ደብዳቤ ነው፡፡ የፍቅሩን ጥሪ መልስ አትንፈግ፡፡ ጌታና አባት፥ ሊሆንህ እስከ መስቀል ሞት የወደደህን ጌታ እየሱስን በመቀበል ፥ ከቅዱሳን ጋር ተቀላቀል፡፡ እግዚአብሔር ይወድሃል

አንድ ቀን ቄሱ በሕዝቡ ፊት እንደ ቆሙ፥ አንድ ወጣት ክርስቶስን ለመከተል ልቡን እንደ ሰጠ አስታወቁ፡፡ በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑን ከሞላው ሕዝብ መሐል የዳነው ወጣት ጓደኛ የሆነ ሌላ ወጣት በታላቅ ደስታ ወደ ላይ ዘለለና በጩኸት ደስታውን ገለጸ፡፡

በሰማይም፦በአንድ ሰው መዳን ይኸ ነው የማይባል ታላቅ ደስታ እንደሚሆን ጌታ ራሱ ነግሮናል፡፡

“እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል፡፡” (የሉቃስ ወንጌል 15፥10)

በአንተ ምክንያት በእግዚአብሔር እና በመላእክቱ ፊት ታላቅ ደስታ ሆኖ ያውቃል? ካልሆነ፥ ዛሬ (ንስሐ በመግባት) ጌታንና መላእክቱን ደስ እንድታሰኝ ፀሎቴ ነው፡፡ አንቺም፡፡

(ዶክተር ደቪድ ጀረማያ ከሚያዘጋጁት መጽሔት ተወስዶ ተተረጎመ)

## ለደኅንነት የንስሐ ፀሎት

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ዛሬ ልቤን ወደ አንተ እመልሳለሁና ተቀበለኝ፡፡ የሞተልኝን ልጅህን እየሱስን አምኜ ተቀበያለሁና ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፡፡ ቃልህን በመታዘዝ እኖራለሁና የመንግሥትህ ወራሽ አድርገህ ተቀበለኝ፡፡ አሜን፡፡

ይህንን ፀሎት ለመጀመሪያ ጊዜ በዕምነት ከፀለይህ፥ ደኅንነትን መቀበልህ ነው፡፡ ዳግመኛ መወለድህ ነው፡፡ ከሆነም ተጨማሪ ምክሮች እንድንልክልህ፦ በፖስታ፥ ወይም በኢ-ደብዳቤ አሳውቀን፡፡ አድራሻችን በመግቢያው ላይ ይገኛል፡፡-- ጌታ ይባረክ፡፡ ጌታ ይባርክህ/ሽ፡፡

* * * * * * * * * 

www.ethioGodslove.org

ዓለም አቀፍ የድር ገጻችንን (www) ይጎብኙ፡፡ በቅርቡ እንደ ጌታ ፈቃድ፥መዝሙሮችንና የድምፅ መልዕክቶችን ማቅረብ እንጀምራለን፡፡ ፀልዩልን፡፡ ምከሩን፡፡

እየሱስ ጌታ ነው፡፡

ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ፡፡